ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፫፣ ሰኔ ፳፻፲፫ ዓ.ም

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት።



ባለድርሻ አካላት የተሻሻለው የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ላይ ግብዐት ለመስጠት ተሰባሰቡ

በዚህ እትም. . .

የተከለሰው የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC) ፪

ዜናዎች ፪

ሁነቶች ፫

የኢትዮጵያ የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ (MRV) ስርዓትና የአፈፃፀም ደረጃ - ክፍል 2 ፯

ልዩ ልዩ ሀትመቶች ፯



ዋና አዘጋጅ፥ ንጉሱ ለማ ገብሬ

አዘጋጆች፥ ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ፣ በእምነት ተሾመ እና ሮቢ ረዳ

አምደኞች፥ መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

ግራፊክስና ሌይአውት፥ አርሴማ አንዳርጋቸው

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፫

ዜናዎች

የተሻሻለው የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ላይ ግብዐት ተሰበሰበ

የተሻሻለው የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ የተለያዩ ባለድርሻዎች አካላት ማለትም የዘርፍ ሚኒስቴር መ/ቤቶች ሀላፊዎች፣ አምባሳደሮች፣ የልማት አጋር አካላት፣ የክልሎች የዘርፉ አመራሮች እና የሲቪል ማህበራት ተወካዮች በተገኙበት የማስተዋወቅና ግብዐት የማሰባሰብ ምክክር፣ በአካልና በበይነ መረብ ታግዞ ሰኔ 24 ቀን 2013 ዓ.ም ተካሂዷል።

የተከለሰው የኢትዮጵያ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ እ.አ.አ. እስከ 2030 የሚተገበሩ ግቦችን ያካተተ ስለመሆኑ በመድረኩ ላይ ተገልጿል። መድረኩን በይፋዊ ንግግር የከፈቱት በኢፌዲሪ የአካባቢ፣ ደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ኮሚሽነር ክቡር ፕ/ር ፍቃዱ በየነ እንዳሉት እቅዱ በ 2030 የሀገራችንን የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን በ 68.8% ለመቀነስ በሚያስችል ሁኔታ የታቀደ ከመሆኑም በተጨማሪ በቀደመው እቅድ ውስጥ ያልተካተቱ 40 የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ተግባራትን ያካተተ መሆኑን ገልጸዋል። ምንጭ

የዳሰሳ ጥናት ውጤቶች፤ በዘመነ ኮቪድ-19 ወቅት የበይነ መረብ ተሳትፎ ውጤታማነት

እ.ኤ.አ. በ 2020 በተካሄደው የ ‹ሲዲኬን› የዳሰሳ ጥናት መሠረት እና በአፍሪካ፣ እስያ እና ደቡብ አሜሪካ ሀገራት ከሚሠሩ የአየር ንብረት ለውጥ ባለሙያዎች ጋር በተደረጉ ቃለ-መጠይቆች፣ በዘመነ ኮቪድ 19 ከቤት ሆኖ በበይነ መረብ አማካይነት ስራዎችን መስራትን በተመለከተ የባለሞያዎችን ልምዶችና ያጋጠሟቸውን ተግዳሮቶች የሚዳስስ ጥናት ይፋ ሆኗል። ጥናቱ በዓለማችን በበየነ መረብ ስራዎችን ከማከናወን ረገድ ምን ያህል ውጤታማ ተሳትፎን ማድረግ እንደሚቻልና መሻሻል ይገባቸዋል ባላቸው ጉዳዮች ላይ የጥናቱ ተሳታፊዎችን ምልከታ ያሳያል። ምንጭ

የተከለሰው የኢትዮጵያ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC)

- በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የተዘጋጀ

በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC) የፓሪስ ስምምነትን በ2007 ዓ.ም የፈረሙ አባል ሀገራት የአየር ንብረት ለውጥን ለመመከት እንዲያስችላቸው ለመተግበር ያቀዱት የድርጊት መርሀ-ግብር ነው። አባል ሀገራቱ ለማሳካት ያሰቡትን የላቀ ዕቅድ በራሳቸው ውሳኔ ከሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታና ቅድሚያ ሊሰጣቸው በሚገባ ጉዳዮች ላይ በመመርኮዝ አንፀባርቀዋል። የሀገራት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDCs) በተባበሩት መንግስታት የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፍ ኮንቬንሽን (UNFCCC) መዝገብ ውስጥ ተቀምጦ ይገኛል።

የፓሪስ ስምምነት አባል ሀገራት በየአምስት አመቱ ቀደም ሲል ካስገቡት NDC እድገት የሚያሳይ እና የሃገራቱን የላቀ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ NDC ለማስገባት ተስማምተዋል። በተያያዘም በፓሪስ ስምምነት መሰረት ኢትዮጵያ በሐምሌ 2013 ዓ.ም ለUNFCCC የሚገባ ከተለምዶ አሰራር (BAU) ጋር ሲነፃፀር በ2022 ዓ.ም የ68.8% የልቀት ቅነሳ ኢላማ የያዘ የNDC ክለሳ ስራን አጠናቃላች።

በፈቃደኛነት ላይ የተሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ የክለሳ ሂደት

NDC የመከለስ ሂደቱ ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ሂደቶች ውስጥ ያለፈ ሲሆን ይህም ሰነዶችን መገምገም፤ መረጃ ማሰባሰብን፤ ሞዴል መስራትን፤ ግኝቶችን ማረጋገጥ እንዲሁም የባለድርሻ አካላትን ማማከርን ያጠቃልላል። በዚህ ሂደት ላይ IPCC 2006 መመሪያ፣ የኢትዮጵያ የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ፣ የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚ የልማት ሞዴል፣ በቅርብ ጊዜ የተካሄደ የእንሰሳት ሀብት ቆጠራ መረጃና የቅርብ ጊዜ የIPCC ዳሰሳ ጥናት ሪፖርት (AR5) ሰነዶችን በግብዐትነት ተጠቅሟል።

የማስተሰረያ (Mitigation) ክፍል የክለሳ ሂደት

የማስተሰረያ ክፍል ቴክኒካዊ የትንተና ሂደቱ የሚከተሉትን አምስት ደረጃዎች የተከተለ ነበር፤

ወደ ገፅ ፫

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ከገፅ ፪ የቀጠለ..

ሀ- ከተለመደው አሰራር (BAU) የሚወጣውን የሙቀት አማቂ ጋዝ የልቀት መጠን የመከለስ ስራ

ለ- የማስተሰረያ ድርጊቶች በመተግበር በ2022 ዓ.ም የሚኖረውን የልቀት ቅነሳ መጠን ማስላት

ሐ- የ2017 እና የ2022 ዓ.ም የልቀት ቅነሳ ሂላማዎችን ማስቀመጥ

መ- ቅድሚያ የሚሰጣቸውን የማስተሰረያ ተግባራትን መለየት እና አፈፃፀም ለመለካት የሚያስችሉ አመላካቾችን የመወሰን ስራ

ሠ - በሀገር ሀብት እና ከአጋር አካላት በሚገኝ ድጋፍ የሚተገበሩ የፖሊሲ አማራጮችን መለየት ናቸው።

የማጣጣሚያ (adaptation) ክፍል የክለሳ ሂደቶች

የማጣጣሚያ ክፍል የክለሳ ሂደት የሚከተሉትን ሰነዶች እንደ ግብዐት ተጠቅሟል፤

ሀ- ሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ

ለ- ሀገራዊው የማጣጣሚያ ዕቅድን ማስተግበሪያ አቅጣጫ

ሐ- ለሀገራዊ የማጣጣሚያ ዕቅድ ትግበራ የሚረዳ ሀብት ማፈላለጊያ ስትራቴጂ

መ- ሀገራዊው የ10-ዓመት የልማት ዕቅድ

ሠ- የተለያዩ ዘርፍ ተኮር የተጋላጭነት የዳሰሳ ጥናቶች

በመቀጠልም ከተለዩት የማጣጣሚያ ዘዴዎች ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸውን በመምረጥና እነዚህንም ለመተግበር የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠን በማስላት የትኞቹን ከሀገር ውስጥ የትኞቹን ደግሞ ከአጋር አካላት በሚገኝ ሀብት እንደሚተገበሩ ተመላክቷል። የስርዓተ-ጾታ እና የተቋማት የአቅም ክፍተት ትንተናም ተካሄዷል።

የተከለሰው NDC የኢትዮጵያን ከዚህ በፊት ከነበረው የተሻለ ቆራጥነት የሚያሳየው ከዚህ ስር በተዘረዘሩት ምክንያቶች ነው።

- ከሀገሪቱ የሙቀት አማቂ ጋዝ መጠን መረጃ እና ከተከለሰው የልቀት ብዜት ጋር በማጣጣም እንዲሁም የIPCCን 2006 መመሪያን በተሻለ ሁኔታ በመከተል ጠንካራ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቅት መንገድና ሂላማ ማስቀመጡ፤
- የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀትን በ68.8% የመቀነስ ሂላማን ማስቀመጡ፤ ይህም ከበፊቱ NDC አንጻር (64%) የተሻለ መሆኑ፤
- የተሟላ የማጣጣሚያ አመላካቾችን፣ መነሻ መረጃ እና የ2022 ዓ.ም ሂላማ ማካተቱ፤ የመጀመሪያው NDC ላይ እነዚህ መረጃዎች አለመኖራቸው፤
- በሀገር ሀብት እና ከአጋር አካላት በሚገኝ ድጋፍ የሚተገበሩ የማጣጣሚያና የማስተሰረያ ዘዴዎች መለየቱ፤ ይህም ከመጀመሪያው NDC ጋር ሲነፃፀር የሀገር ውስጥ ድርሻ የተሻለ መሆኑ፤
- በNDC የትግበራ ጊዜ ውስጥ የተሻለ ቆራጥነትን የሚያሳዩ አማራጭ ለማፈላለግ መገለጹ፤
- ክለሳው ላይ የተጠቀምንባቸው መሳሪያዎች ምቹ ሁኔታን ስለሚፈጥሩ እና ወደፊት ከሚኖር የፖሊሲ ለውጥና ውጫዊ አደጋዎች ጋር ለማጣጣም ምቹ መሆኑ፤
- የተሻሻለ የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ/የክትትልና ግምገማ ስርዐት በመከተል የማስተሰረያና የማጣጣሚያ ትግበራ ደረጃን ለመለካት የሚያስችል የተሻለ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩ ናቸው።

የሀብት ፍላጎት እና የአተገባበር ሁኔታዎች

በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ዕቅድ (NDC)ን በቀጣይ አሰርት ዓመታት ለመተግበር 316 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልጋል። ከዚህ ውስጥ የማስተሰረያ ተግባራት የ275.5 ቢሊዮን ዶላርና የማጣጣሚያ ተግባራት ደግሞ 40.5 ቢሊዮን ዶላር ድርሻ አላቸው።

20% የሚሆነው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ቅነሳ ተግባራት ወጪ የሚሸፈነው በሀገር ውስጥ ሀብት ሲሆን ቀሪው 80% ደግሞ ከለጋሽ አካላት በሚገኝ ገንዘብ የሚሸፈን ይሆናል። በዚህም መሰረት ኢትዮጵያ እስከ 2022 ዓ.ም ድረስ 63.2 ቢሊዮን ዶላር ለአየር ንብረት ለውጥ የማስተሰረያና የማጣጣሚያ ተግባራትን ለመፈፀም የምትመድብ ሲሆን፤ ይህም በአመት በአማካይ 6.32 ቢሊዮን ዶላር ይገመታል። ቀሪ ተግባራትን ለማስፈፀም የሚያስፈልገው 252.8 ቢሊዮን ዶላር ደግሞ ከለጋሽ አካላት መሰብሰብ ይኖርበታል።


ወደ ገፅ ፬

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ከገፅ ፫ የቀጠለ

ኢትዮጵያ በፓሪስ ስምምነት ላይ በተገለፁት የካርቦን ገበያ ላይ በመሳተፍ ከዘርፉ ከሚገኙ ዕድሎች ለመቋደስ ከፍተኛ ፍላጎት አሳይታለች።

የተከለሰው ከተለመደው አሰራር (BAU) የሚወጣው የልቀት መጠን፣ በለጋሽ አካላት ድርሻና በሀገር ውስጥ ሀብት የሚከናወኑ ተግባራት




ምስል 1 - የኢትዮጵያ ከተለመደው አሰራር (BAU) የሚወጣው የልቀት መጠን፣ በለጋሽ አካላት ድርሻና በሀገር ውስጥ ሀብት ከሚከናወኑ ተግባራት የልቀት መጠን አቀናነስ

በመጀመሪያው NDC ከነበረው በተለመደው አሰራር (BAU) ከሚኖረው የመነሻ ዓመት የልቀት መጠን፤ ከተከለሰው NDC ጋር ሲነፃፀር ልዩነት ያለው ሲሆን ይህም የሆነበት ምክንያት በክለሳው ሂደት ጥቅም ላይ በዋለው የተለየ የአገማመት ዘዴና አዳዲስ ዳታዎች ምክንያት ነው።

የተከለሰው የመነሻ ዓመት (2002 ዓ.ም) የልቀት መጠን 247 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e ሲገመት ይህም የተለመደው አሰራርን ብንከተል በ2022 ዓ.ም 404 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e ይደርሳል። በሀገር ውስጥ በሚገኝ ሀብት የማስተሰረያ ስራዎች ትግበራ 347 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e በ2022 ዓ.ም የልቀት መጠን ሲኖር ይህም የ14% ወይንም የ56 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e ቅነሳ ይሆናል። በለጋሽ አካላት ድጋፍ የታቀዱ ተግባራት ደግሞ በ2022 ዓ.ም የሚኖረው የልቀት መጠን ወደ 125.8 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e የሚያወርዱት ሲሆን ይህም ከተለመደው አሰራር ጋር ሲነፃፀር የ68.8% ወይም የ277.7 ሚ.ሜ.ቶን CO_2e ቅነሳ ይሆናል።

ዘርፎች ለኢትዮጵያ የአማቂ ጋዞችን የማስተሰሪያ (mitigation) ግቦች ያላቸው ድርሻ


ከዚህ በታች ያለው ምስል ዘርፎች ለየአማቂ ጋዞችን ልቀት ማስተሰሪያ ግቦች ያላቸውን ድርሻ በንፅፅሮሽ ያስቀምጣል።



ምስል 2፡ ዘርፎች ለየአማቂ ጋዞችን ልቀት ማስተሰሪያ ግቦች ያላቸውን ድርሻ

በተከለሰው NDC ውስጥ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ተግባራት ድርሻ

የተከለሰው NDC በሀገር ውስጥና በለጋሽ አካላት የሚተገበረውን መጠን በግልጽ በመለየት 40 የማጣጣሚያ ተግባራትን ለይቷል። እነዚህም ተግባራት የግብርና፣ የደን፣ የውሀ፣ የትራንስፖርት፣ የከተማ፣ የጤና፣ የመሬት አስተዳደር፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማት፣ የአየር ንብረት አገልግሎት እና የአደጋ መከላከል ዘርፎችን ያጠቃልላል።



ምስል 3፡ በየዘርፉ የታቀዱ የማጣጣሚያ ተግባራት

ወደ ገፅ ፭

ሁነቶች


የኮቪድ 19 ወረርሽኝ በዓለማቀፍ ደረጃ መከሰቱንና በፍጥነት መስፋፋቱን ተከትሎ በርካታ የአየር ንብረት ለውጥና ዘላቂ የአካባቢ ልማትና ጥበቃን የተመለከቱ ሁነቶች በመረጃ ቴክኖሎጂ በመታገዝ እየተካሄዱ ናቸው። የሚከተሉት በበይነ መረብ አማካይነት የሚከናወኑ ሁነቶች ለማናቸውም ታዳሚዎች ተደራሽ ናቸው። እያንዳንዱን ሁነቶች አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎ ‹ምንጭ› የሚለውን ማስፈንጠሪያ ይክፈቱት።

- የአየር ንብረት የፈጠራ መድረክ 2021፣ ክላይሜት አክሽን፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ
- በአለም አቀፍ የደን ጥበቃ የደን ጭፍጨፋን ለመመርመር ከሳተላይት የተወሰዱ ምስሎችን መጠቀም፣ ደብልዩ. አር. አይ፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ
- ተፈጥሮን በማንአለኝበት ማረቅ፣ ክላይሜት ዋን፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ
- የተባበሩት መንግስታት የምግብ ስርዓቶች ቅድመ-ጉባኤ 2021፣ የተባበሩት መንግስታት ፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ
- ክፍለ አህጉራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ሳምንት (ጭብጥ ክፍለ-ጊዜ)-አፍሪካ፣ ክላይሜት ሊንክስ፣ ሐምሌ 2021 | ምንጭ
- የአየር ንብረት ለውጥ ማስተሰሪያዎችን ከአየር ንብረት ደህንነት አኳያ መረዳት፣ ክላይሜት ሊንክስ፣ ነሐሴ 2021 | ምንጭ
- የእስያ-አፍሪካ የበይነ መረብ ሥልጠና መርሃ-ግብር፤ የውሃና የቆሻሻ መረጃዎች ለመወያየት እና ለመተግበር በሚያቀል መለኩ ማቅረብ፣ የሳይንስና አካባቢ ማዕከል፣ ነሐሴ 2021 | ምንጭ
- የከተሞች የሽግግር ጉባኤ፣ ክላይሜት አክሽን፣ መስከረም 2021 | ምንጭ
- የዘላቂ ፈጠራ መድረክ 2021፣ ክላይሜት አክሽን፣ ህዳር 2021 | ምንጭ

ከገፅ ፩ የቀጠለ..

የNDC ትግበራን ውጤታማነትን የመለኪያ የመዘገቢያና ማረጋገጫ (MRV) ዘዴ

የNDC ክለሳ አረንጓዴ ኢኮኖሚ ሞዴልን መሰረት ካደረጉት የኢትዮጵያ የ10-ዓመት የልማት ዕቅድና ከ2050 ስትራቴጂ ጋር የተጣጣመ ነው። የልቀት ቅነሳና የማጣጣሚያ ተግባራት በ10-ዓመት ትግበራ በተቀመጠው የMRV ስርዓት መሰረት በዘርፎች የክትትልና ማረጋገጫ ስራ ይከናወናል። የሚከተለው ጠቅለል ያለ የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍን ያመላክታል።



ምስል 4፡ NDC ተኮር የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ እንዲሁም የክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ

የኢትዮጵያን NDC ለመተግበር የሚያስፈልጉ የአቅም ግንባታ እና የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች

በተከለሰው NDC ስር የተለዩትን የማስተሰረያና የማጣጣሚያ አማራጮችን ለመተግበር ከገንዘብ በተጨማሪ ኢትዮጵያ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ድጋፎችን ትፈልጋለች።

- የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ ስርዓትን (MRV) እና ለዚህ የሚያስፈልጉ ተቋማትን በሰው ሀይልና መሰረተ ልማት ማጠናከር፤
- የበጀት ፍሰትን በዝርዝር ለመለየት የሚያስችል የህዝብ ወጪ መገምገሚያ ማዕቀፍ በሁሉም የመንግስት ድርጅቶች እና በሁሉም ደረጃዎች፤
- የልኬት፣ ዘገባና ማረጋገጫ እና የክትትልና ግምገማ ስርዐቱን ከስታስቲክ መረጃ አስተዳደር ጋር ማስተሳሰር፤
- የመረጃን ተደራሽነትን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ማረጋገጥ፤
- በዘርፎችና በክልሎች መካከል ያለውን የስራ ግንኙነት በማጠናከር ለNDC የተሻለ አተገባበር፣ ክትትል እና ግምገማን ማረጋገጥ
- እንደ አረንጓዴ የሲሚንቶ የምርት ሂደት፣ የቅድመ-ማስጠንቀቂያ ስርዐት፣ ዘላቂ የተፋሰስ ልማትና የመሬት አጠቃቀም አስተዳደር ያሉ የቴክኖሎጂ ሽግግሮችን ማስፋፋት ናቸው።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፫


ልዩ ልዩ ሀትመቶች

ለስርዐተ ፆታ ጥያቄዎች ምላሽ ሰጪ የሆነ በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖዎች መቀነሻ ዕቅድን ማዘጋጀት




ይህ መመሪያ በዋናኝነት ለመንግስት ተወካዮች፣ ለአገር ውስጥ አስተባባሪዎች እና አማካሪዎች የተዘጋጀ ነው። መመሪያው የሥርዓተ-ፆታ እኩልነትን ከግምት ውስጥ ለማስገባት የሚደረጉ ጥረቶችን ለማበረታታት የሚረዱ አምስት ነጥቦችን የያዘና የሥርዓተ-ፆታ መተግበሪያዎች እና የአሰራር ዘዴዎች እንዴት ለስርዐተ-ፆታ ምላሽ የሚሰጡ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ የድርጊት መርሃ-ግብሮችን ለማዘጋጀት እንደሚስችሉ ለማሳየት ታስቦ የተዘጋጀ ነው ። [ምንጭ]

የውሃ ምርታማነት ፣ የምርት ክፍተት እና የተመጣጠነ ምግብ በኢትዮጵያ



ይህ ዘገባ የውሃ እና የአልሚ ምግቦችን ግንኙነትን ከኢትዮጵያ ከተገኙ የምርት፣ የውሃ ምርታማነት እና በምግቦች ውስጥ የሚገኙ በብዛት እና በአነስተኛ መጠን የሚያስፈልጉ ንጥረ ነገሮች መረጃዎችን በመጠቀም ይመረምራል። [ምንጭ]

ያልተነገረው የዓለም አካባቢ ጥበቃ መሪ ተቋም ታሪክ፤ የተ.መ.ድ. የአካባቢ ፕሮግራም የ50 ዓመት ጉዞ



ማሪያ ኢቫኖቫ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተ.መ.ድ. የአካባቢ ፕሮግራም (UNEP) የአቀራረጽ ጉድለት አለበት የሚለውን የተለመደ ትችት በመቃወም ተቋሙ የተሰጠውን ተልእኮ (ሙሉ በሙሉ ባይሆንም) ተግባራዊ ማድረጉን ይሞግታሉ። በመሆኑም ኢቫኖቫ፣ የተ.መ.ድ. የአካባቢ ፕሮግራም ሃምሳኛ ዓመቱን ሲያከብር ጊዜው ራሱን እንደገና የሚያድስበት እድልን ይፈጥራል ይላሉ። [ምንጭ]

የኢትዮጵያ የሙቀት አማቂ ጋዞች የመለኪያ፣ መዘገቢያና ማረጋገጫ (MRV) ስርዓትና የአፈፃፀም ደረጃ - ክፍል 2

የአዲስ አበባ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ዝርዝር መረጃ

- በንቲ ፈርዲሳ ዱጋሳ፣ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን ብሄራዊ የሙቀት አማቂ ጋዞች ስረዐት ዝርጋታ ዳይሬክተር

[የአዲስ አበባ የ2008 ዓ.ም የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ዘገባ] በC40 እና በሪካርዶ የኢነርጂና አካባቢ ድርጅት ድጋፍ በአዲስ አበባ የአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ ልማት ኮሚሽን በ2012 ዓ.ም ተከናውኗል። የጥናቱ ሰነድ የተዘጋጀው አዲስ አበባን ከሌሎች 11 ከተሞች ተረታ ባስቀመጠው የ C40 የአለም የአየር ንብረት የድርጊት መርሀ-ግብር መሰረት ነው።

ጥናቱ የከተማውን የ2008 የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን በዝርዝር ያስቀመጠ ሲሆን በC40-ከተሞች የአለም አቀፍ በማህበረሰብ ደረጃ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት ፕሮቶኮልን መሰረት ያደረገ ነው። የጥናቱ ውጤትም ሪፖርት የተደረገው በC40 የከተሞች የልኬት ዘገባና ኢንፎርሜሽን ስርዐት መሰረት ነው።

በየዘርፉ ያለው የልቀት መጠን አጠቃላይ መረጃ

በአዲስ አበባ በ2008 ዓ.ም የ14.48 ሚ.ሜ.ቶን የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት እንደነበረ ተገምቷል። ከዚህም ውስጥ የትራንስፖርቱ ዘርፍ 78% የልቀት መጠን በመያዝ ከፍተኛውን ድርሻ ሲይዝ በመከተልም ከቆሻሻ የሚወጣው ልቀት 13% እንዲሁም ተንቀሳቃሽ ያልሆኑ ኢነርጂ ዘርፍ የ8% ድርሻ ነበራቸው።


የትራንስፖርቱ ዘርፍ ከፍተኛ ልቀት ሊኖረው የቻለበት ምክንያት በከተማው ያረጁ መኪኖች መኖራቸው እና የአየር መንገድ (Scope 3) ልቀት በልኬቱ ውስጥ በመካተቱ ነው። ይህ ደግሞ ባጠቃላይ የዘርፉን 69% ድርሻ ይይዛል። በቆሻሻ አወጋገድ ዘርፍ፣ ከከተማው የሚወጣውን ደረቅ ቆሻሻ በገላጣ ቦታዎችና በማሸን በመታገዝ ማቃጠል ዋናዎቹ የልቀት ምንጮች ሲሆኑ የባዮማስ ኃይልን ከመጠቀም የሚወጣው ልቀት ደግሞ የማይንቀሳቀሱ የኢነርጂ ዘርፍ ለሚባሉት ዋነኛ የልቀት ምንጭ ነበር።

ወደ ገፅ ፮

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፪፣ ቁጥር ፫

ከገፅ ፮ የቀጠለ...



ምስል 1፡ አጠቃላይ የነፍስ ወከፍ ልቀትና የዘርፎች የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ድርሻ

የትራንስፖርት ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መረጃ


የመንገድ፣ ከመንገድ ውጪ፣ ባቡር፣ ውሀ እና አየር፤ ጭነት እና መንገደኞችን ማመላለሻ ከሆኑት ዋነኛ ዘዴዎች ናቸው። በአዲስ አበባ ዋነኛ የትራንስፖርት ዘዴዎች ተሽከርካሪዎች ናቸው። በተጨማሪም በከተማው በኤሌክትሪክ የታገዘ የባቡር ትራንስፖርት 34.5 ኪ.ሜን ይሸፍናል። የአየር ትራንስፖርት አዲስ አበባን ከሀገር ውስጥ እና ከአለም አቀፍ ከተሞች ጋር ያገናኛታል።

ከመንገድ ውጪ ያለው የትራንስፖርት ዘርፍ ጠቀሜታ ላይ የሚውለው ለፋብሪካ ምርት፣ ለግንባታ እና ለግብርና ዘርፎች ነው። ከትራንስፖርት ዘርፍ የሚወጣው ልቀት ምንጩ ከተቃጠለ ነዳጅ ወይም በመስመር የሚደርሰውን የኤሌክትሪክ ሀይልን ከመጠቀም ነው። የትራንስፖርቱ ዘርፍ በ2008 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከነበረው የ78% የልቀት ድርሻ፣ የመንገድ ትራንስፖርትና የአየር መንገድ በቅደም ተከተል የ66% እና የ34% ድርሻ ነበራቸው።

ከመንገድ ውጪ ያሉ ትራንስፖርቶች እና የባቡር መንገድ ዝቅተኛ ድርሻ ነበራቸው። ተሽከርካሪዎች 7,461,886 ቶን የካርቦንዳይ አክሳይድ እኩሌታ በመልቀቅ ከፍተኛውን የልቀት ቦታ ሲይዙ ከዚህም ውስጥ የናፍጣ ተሽከርካሪዎች የ58% ድርሻ ሲኖራቸው፤ የቤንዚን ተሽከርካሪዎች 42% ድርሻ ነበራቸው።

የአየር መንገድ ዘርፍ ደግሞ ከጀት ቤንዚን ከሚወጣ 3,808,250 ቶን ልቀት በሁለተኛ ቦታ ላይ ይቀመጣል። የትራንሰፖርቱን ዘርፍ ልቀት ለመለካት እንዲያስችል ከዚህ ስር በተዘረዘሩት 3 ክፍሎች ተከፍሏል፤

- **Scope 1** - ናፍጣ፣ ቤንዚን፣ እና ለመንገድ ተሽከርካሪ የሚውሉ LPG ነዳጆችን ያጠቃልላል። ልቀቱ የተሰላው ከላይ ወደ ታች ሽያጩ በሚከናወንበት አግባብ ነው።
- **Scope 2** - በመስመር አቅርቦት የታገዘ ሀይል። የኤሌክትሪክ ባቡር ልቀት በ2008 ዓ.ም በጣም ዝቅተኛ ነበር።
- **Scope 3** - ይህ የአየር መንገድን እና በመንገድ ላይ ድንበር ተሻጋሪ ትራንስፖርትን ያጠቃልላል።



ምስል 2፡ በተለያዩ ስኮፖች ከትራንስፖርት ዘርፍ በ2008 የነበረው ልቀት

የመንገድ ትራንስፖርት

የመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ከአጠቃላዩ 11,263,787 ቶን ካርቦንዳይ አክሳይድ እኩሌታ 66% ድርሻ ይይዛል። ከናፍጣ መኪና የሚወጣው 6,504,385 ቶን የካርቦንዳይ አክሳይድ እኩሌታ (87%) ሲይዝ ከቤንዚን የሚወጣው 951,150 ቶን የካርቦንዳይ አክሳይድ እኩሌታ ደግሞ 13% ይይዛል። ከመንገድ የትራንስፖርት አገልግሎት ከ10 ኩንታል በላይ የሚይዝ የደረቅ ጭነት አገልግሎት ለልቀት ከፍተኛ ድርሻ ሲኖረው ይህም 3,454,950 ቶን የካርቦንዳይ አክሳይድ እኩሌታ ነው።


ወደ ገፅ ፭

ከገፅ ፪ የቀጠለ...

ተሳታች ተሸከርካሪ፣ ከ12 ሰው በታች የሚይዙ አውቶብሶችና ከ10 ኩንታል በታች የሚይዙ የደረቅ ጭነት መኪኖች በቅደም ተከተል 862,429.2፣ 747,041.0 እና 712,024.6 ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ በመያዝ ይከተላሉ። የ3 ጎማ የደረቅ ጭነት አገልግሎት 23.7 ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ በመያዝ ዝቅተኛ የልቀት ድርሻ ይይዛል።

ስኮፕ 1 የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት 6.64 ሚ.ሜ.ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ ሲኖረው፣ ይህም በከተማዋ ውስጥ የተካሄዱ የትራንስፖርት እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል።

ስኮፕ 3 ደግሞ 814,298 ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ ሲኖረው ከከቶሞች ውጪ ያለውን ድንበር ተሸጋሪ የትራንስፖርት ክፍል ይይዛል። እነዚህ ከከተማዋ የሚነሱ ውይም መድረሻቸው አዲስ አበባ የሆኑ ጉዞዎችን ያጠቃልላሉ። የደረቅ ጭነት ማጓጓዣ፣ ተሳታች መኪና፣ አውቶብስ እና የቤት መኪና በቅደም ተከተል ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ።




ምስል 3፡ የልቀት መጠን በተሸከርካሪዎች አይነት

ከቆሻሻ የሚወጣው የልቀት መጠን ዝርዝር

የከተማ የቆሻሻ አወጋገድ አስተዳደር ኢጀንሲ ከከተሞች የሚወጣውን ቆሻሻ አወጋገድ የማስተባበር ሀላፊነት አለበት። ቆሻሻው በማህበራት ከቤቶችና ከንግድ ድርጅቶች ይሰበሰባል። አንዳንድ አካባቢዎች ላይ የዝውውር ጣቢያዎች አሉ፤ እነዚህም ከተለያዩ ምንጭ የሚመጡ ቆሻሻዎችን ለመለየት ይረዳል። በከተማው ቆሻሻን ለመጣል ሲያገለግሉ የቆዩ ከ50 ዓመታት በላይ ያገለገሉ ክፍት የቆሻሻ መጣያ ስፍራዎች አሉ።

በ2008 ዓ.ም ከከተማው የወጣው የቆሻሻ መጠን 720,761 ቶን ነው። ከከተማው ከሚወጣው ቆሻሻ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው የኦርጋኒክ ቁሳቁስ ሲሆን ይህም 64% ይሸፍናል። የተቀረው ፕላስቲክ፣ ብረታ ብረትና ወረቀትን ይጨምራል።




ምስል 4፡ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት፤ በቆሻሻው አይነት

ሪፖርቱ ያጠቃለላቸው ሌሎች ዘርፎች የኢንዱስትሪ የምርት ሂደትና ምርት አጠቃቀም (IPPU) እና ግብርና፣ ደንና ሌሎች መሬት አጠቃቀም (AFOLU) ናቸው። በ2008 ዓ.ም ከኢንዱስትሪ የወጣው 11,434 ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ የልቀት መጠን በ2004 ዓ.ም ከወጣው 10,514.5 ቶን ጋር ሲነፃፀር አነስተኛ ጭማሪ አለው። የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት በ4% የመቀነስ አዝማሚያ ሲያሳይ የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ልቀት በአንድ ዩኒት ጂዲፒ በአብዛኛው የመጨመር ሁናቴ ያሳያል።

የAFOLU ተግባራት በ3 ክፍል ሲከፈሉ እነዚህም የእንሰሳት፣ የመሬት እና ሌሎች የተጠቃለሉ የካርቦን ዳይ ኦክሳይድ ምንጮች እና ከካርቦንዳይ ኦክሳይድ ውጪ ያሉትን የጋዝ ምንጮችን ያጠቃልላል። ከAFOLU የሚወጣው የሙቀት አማቂ ጋዞች ሜቴን፣ ናይትረስ ኦክሳይድ እና ካርቦን ዳይ ኦክሳይድን ይይዛል። የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ስሌት ዘዴ በGPC ላይ በተቀመጡት ምክረ ሀሳብ መሰረት የተካሄደ ነው። ሁሉም በእንሰሳት እርባታ ዙሪያ የሚካሄዱት ተግባራት በከተማው ወሰን ውስጥ በመሆናቸው ምክንያት ከዚህ የሚወጡት የሙቀት አማቂ ጋዞች በስኮፕ-1 ውስጥ የተካተቱ ናቸው። ከአዲስ አበባ ከAFOLU ዘርፍ በ2008 ዓ.ም የወጣው አጠቃላይ የሙቀት አማቂ ጋዝ 141,329 ቶን የካርቦንዳይ ኦክሳይድ እኩሌታ ነው።

ወደ ገፅ ፬


ከገፅ ፮ የቀጠለ..



ምስል 5፡ በአዲስ አበባ ከAFOLU ዘርፍ የወጣው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት

በፊት ከተካሄደው ልኬት ጋር ያለው ንፅፅሮሽ


በ2008 ዓ.ም የተካሄደው የአዲስ አበባ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት ከ2004 ዓ.ም ከተካሄደው ጋር ሲነፃፀር የ50% ልቀት ጭማሪን ያሳያል። ይህም ሊሆን የቻለው ከትራንስፖርትና ከቆሻሻ የሚወጣው የልቀት መጠን በቅደም ተከተል የ66% እና የ13% ጭማሪ በማሳየታቸው ነው።



ምስል 6፡ የ2004 ዓ.ም እና የ2008 ዓ.ም የአዲስ አበባ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ንፅፅሮሽ

ከሌሎች ከተሞች ጋር ያለው የልቀት ንፅፅሮሽ

ከአዲስ አበባ ከተማ በ2008 ዓ.ም የወጣው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት እንደ ኦክላንድ (ኒውዚላንድ) ፣ ኬፕታውን (ደቡብ አፍሪካ)፣ ደርባን (ደቡብ አፍሪካ)፣ ዳካር (ሴኔጋል)፣ ጓድላሃራ (ሜክሲኮ)፣ አቴንስ (ግሪክ) እና ኦስትን (አሜሪካ) ጋር የተነፃፀረ ሲሆን በዚህም መሰረት የአዲስ አበባ የትራንስፖርት ዘርፍ ልቀት ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ሲሆን ከቆሻሻ የሚወጣው ልቀት ደግሞ በከፍተኛነት ከተዘረዘሩት መሃከል ይገኛል። የአዲስ አበባ የነፍስ ወከፍ የልቀት መጠን አነስተኛ ከሚባሉት መሃከል ሲገኝ፣ በ1000 ዶላር ጂዲፒ ያለው ልቀት ግን ከፍተኛ ከሚባሉት ተርታ ይገኛል።



ምስል 7፡ በዘርፎችና በነፍስ ወከፍ በአዲስ አበባና ሌሎች ትላልቅ ከተሞች ያለው ልቀት

ማጠቃለያ

የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ልኬት የተካሄደው የከተማውን በ2022 ዓ.ም ለአየር ንብረት አልበገሬነትና ዘላቂ ዕድገትን ለማረጋገጥ ያለውን ዓላማ ለመደገፍ ሲሆን ይህም ሀገራዊው ለአየር ንብረት የማይበገር አረንጓዴ ኢኮኖሚ ግቦችና የፓሪስ ስምምነትን ለማሳካት አስተዋፅኦ ይኖረዋል።ንየከተማው የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠንን ለማስላት የGPC እና የIPCC 2006 (እ.አ.አ) መመሪያዎች ጥቅም ላይ ውለዋል። የልቀት ልኬት ዘገባው እንደ ትራንስፖርት፣ የሃይል አጠቃቀም እና ቆሻሻ ከመሳሰሉ ምንጮች ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን የበካይ ጋዝ ልቀትን እንደ ማሳያ ለማቅረብ አስችሏል።

የ2008 የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ዝርዝር መረጃ የከተማውን የ2022፣ 2032 እና 2042 ዓ.ም የልቀት ቅነሳ ዒላማ ለማዘጋጀትና ይህንንም የአየር ንብረት የድርጊት መርሐ-ግብር ላይ ለማስቀመጥ ይረዳል። በሪፖርቱ ላይ ለተካተቱ እና መሰረታዊ ለሆኑ ዘርፎች የአየር ንብረት ተግባራትና የልቀት ቅነሳ ኢላማ የሚቀመጥ ሲሆን አፈፃፀማቸውም ላይ ክትትል ይደረጋል። ይህም ከተማዋ ከልቀት የፀዳች እና ለአየር ንብረት የማትበገር፣ እንዲሁም ነዋሪዎቿ ከማህበረሰባዊ-ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ጠቀሜታ ተቋዳሽ እንዲሆን ያስችላል።

ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

የኢፌዲሪ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን

ሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት

ፖ.ሳ.ቁ : 12760, አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ስልክ ቁጥር: +251 11-170-4038/4150

ኢሜል: efcccethiopia@gmail.com

ድረ ገፅ: https://www.efccc.gov.et

ሀላፊነት ስለመውሰድ

በዚህ ህትመት ውስጥ የተካተቱ ይዘቶች የግድ የኢትዮጵያን መንግስት ኦፊሴላዊ አመለካከቶችና ፖሊሲዎች የሚወክሉ አይሆኑም። በተጨማሪም ሌሎች ሀገራትንና ተቋማትን የሚመለከቱ አንዳንድ ይዘቶች ቢኖሩ እነዚህ ሀገራቱን የተመለከቱ ጉዳዮች የሀገራቱን የህጋዊ መብት የሀገር ድንበር፣ ወይም ከተማና የስልጣን ሁኔታዎች የኢትዮጵያ መንግስትንም ሆነ ህትመቱን በገንዘብና በቴክኒክ የደገፉ ተቋማት ፖሊሲዎች ወይም አቋሞችን የሚወክሉ አይደሉም።

ስራውን የደገፉ አካላት

NDC PARTNERSHIP | IN CONTRIBUTION TO THE NDC PARTNERSHIP

MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS OF DENMARK | Federal Ministry for Economic Cooperation and Development | Supported by: Federal Ministry for the Environment, Nature Conservation and Nuclear Safety | based on a decision of the German Bundestag | Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands | Norwegian Ministry of Climate and Environment | Norwegian Ministry of Foreign Affairs | Government Offices of Sweden Ministry for Foreign Affairs | UK Government

CDKN Climate & Development Knowledge Network | SOUTH SOUTH NORTH TOWARDS CLIMATE RESILIENCE

Funded by

Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands

IDRC · CRDI International Development Research Centre Centre de recherches pour le développement international

Canada

This work was carried out with the aid of a grant from the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands and the International Development Research Centre (IDRC), Canada, as part of the Climate and Development Knowledge Network (CDKN) Programme. The views expressed herein do not necessarily represent those of the Ministry of Foreign Affairs of the Netherlands, or of the International Development Research Centre (IDRC) or its Board of Governors, or of the entities managing CDKN.